## ምንድን ነው?

አንደ ጽጌ ረዳ . . .
ህይወት ጣር ሆኖባት አይከፈል እዳ
ውበት ውስጧ አርግዛ በጊዜ ተገድዳ
ወራቱን ጠብቃ እስከምትፈነዳ
ፍጥረት ቢጠብቅም . . .

ሰማያት ተቀድደው . . .
ከዋክብትም ቁልቁል አንዳቧራ ረግፈው
አንደ ጥቅምት ጠልም ድንገት ተንጠባጥበው
ሁሉን ቢሸፍኑም . . .

ከምድር አሸዋ ከለሊት ከዋክብት . . .
ከቀላይ መነደል ከውቅያኖስ ሙላት
በሰው ልብ ክሞላው ከምድራዊው ምኞት
የሚበልጥ ቢኖርም . . .

ለምስኪኑ ሰው ግን ስጋ ለለበሰው . . .
ለፈራሹ ገላ ሞት ለሚያሳድደው
ቀኝ ከሌት ሳይታክት ለሚከታተለው
ሮጦ መደበቂያ መሸሻ ማምልጫው
ሰኮናው ምንድን ነው?

*Zewdu Michael*
*2010*

## የዘመን ቃል ኪዳን

በድቅድቅ ጨለማ
ድምጽ ሳይሰማ

ሁሉ በተኛበት
በተቆለፈ አይን በደከመ ጉልበት
ፍጥረት ዝም ባለበት

በዝምታ ቃላት ቀን ለቀን ያወራል
ትላንትና ዛሬን ለነገ ያማዋል
ሚስጥር ይነግረዋል . . .

ን ግ ግ ር  ግን የለም
ድ ም ጽ ም  አይሰማም

ተጠቅልሎ አስከሚያልፍ ሰማይ እንደ ድንኳን
ስርአቱ ይህ ነው የዘመን ቃል ኪዳን

*Zewdu Michael*
*201*

*ማነው?*

*ማእበሉ እየሳቅ*
*በባህር ላይ ሮጦ እየፈነደቀ*

*በሃይል በጉልበቱ*
*ታምኖ በብርታቱ*

*እንደኖህም ዘመን*
*ምድርን እንዳይሸፍን*

*እንደመጣ ሮጦ*
*በባህር ዳር ድንጋይ አለት ተፈጥፍጦ*
*ባሸዋ ውስጠ ሰምጦ*

*እንዲቀር ያረገው*
*በቀስተ ደመናመ ገድቦ እሚያቆመው*
*በቃል ኪዳን ልጓም ቀፍድዶ የሚያስረው*
***ሃይሉ የበረታ ክንደ ብርቱ ማን ነው?***

*በመሬት እንብርት ውስጥ የታፈነው እሳት*
*ገሞራው ገንፍሎ ፈንቅሎ በመውጣት*
*ምድርን እንዳይውጣት*
*እንደ ምንቸት ችሎ ክድን የሚያደርገው*
***ባለሞያው ማን ነው?***

*በመሬት መንቀጥቀጥ የተካበው ሁሉ ወደ ምድር ወርዶ*
*ባንድ ጊዜ ተንዶ*
*እንዳይጨፈልቀው*
*ህይወትን ከምድር ጨርሶ እንዳይፍቀው*
*በልጓም አግዶ ቀፍድዶ እሚያቆመው*
***ፈረሰኛው ማን ነው?***

*Zewdu Michael*
*2010*

**Back to Meskot**

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot**. You may contact Zewdu Sahlu for comments at** zewdu_michael@yahoo.com*